## 6 በበሽታው መያዙን የጠረጠረ ሰው ምን ማድረግ አለበት?

- በዚህ በሽታ መያዝዎን ከጠረጠሩ በፍጥነት በአከባቢው ወደሚገኝ ጤና ተቋም በመሄድ የህክምና እርዳታ ማግኘት አለቦት። ከመታመምዎ 14 ቀናት በፊት በበሽታው ወደተጠቁ አገራት ሄደው ከሆነ ይህንንም ለጤና ባለሙያው ያስረዱ፤
- በሚያስሉበትና በሚያስነጥሱበት ጊዜ በሽታው ወደ ጤነኛ ሰው እንዳይተላለፍ አፍና አፍንጫዎን በመሃረብ ወይም በሶፍት ይሸፍኑ እንዲሁም እጅዎን ሁልጊዜ በውሃና በሳሙና ይታጠቡ።
- የሳል ምልክቱ እስኪጠፋ ድረስ ሰዎች በብዛት የተሰበሰቡበት ቦታ ባይንቀሳቀሱ ከተቻለም ብቻዎትን ይሁኑ፤
- የህመም ስሜቶቹ እስኪጠፉ ድረስ ቢቻል ብቻዎትን በመሆን፤ የመመገቢያ ዕቃዎችንና መኝታዎትን ለብቻ በመጠቀም እንዲሁም የቤት መስኮት በመክፈት በቂ አየር ቤት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ በሽታው ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ መከላከል ይችላሉ።

## 7 ሪፖርት አደራረግ

- ማንኛውም ሰው ትኩሳት ፣ ሳል ፣ የትንፋሽ መቆራረጥና የመተንፈስ ችግር እራሱ ካጋጠመው ወይም በአከባቢው ሌላ ተመሳሳይ ችግር ያለበት ካየ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ ጤና ተቋም ያሳውቁ ወይም በሚከተሉት የስልክ ቁጥሮች ይደውሉ።

እናመሠግናለን።

የጤና ጥበቃና አጋሮቹ

ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት
የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር መዕከል
ስልክ: +251 11 275 8631
+251 11 276 5340
ፋክስ: +251 11 275 8634
ኢሜል: PHEMcenter@ehnri.gov.et
ድህረ ገፅ: http://www.ehnri.gov.et

# የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov)

# የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov)

## 1 የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov) ምንድነው?

የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov) ስሙ እንደሚያመለክተው በመካከለኛው ምስራቅ በሚገኙ በሚከተሉት አገራት፡-

- ሳኡዲ አረቢያ
- የተባበሩት የአረብ ኢሚሬት
- ኳታር
- አማን
- ዮርዳኖስ
- ኩዌት
- የመን
- ሊባኖስ እና
- ኢራን

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተ አዲስ የመተንፈሻ አካል በሽታ ነው። በነዚህ አገራት በሽታው በብዙ ሰዎች ላይ ህመምና ሞት እያደረሰ ይገኛል።

በሽታው የሚመጣው ኮሮና በሚባል ቫይረስ (በአይን በማይታይ ረቂቅ ጀርም) አማካይነት ነው። በሽታው ምንም እንኳን በቂ ፈዋሽ ህክምና እና ክትባት ባይገኝለትም በበሽታው እንዳይዘን ግን መከላከል ይቻላል።

በአገራችን በሽታዉ ያልተከሰተ ቢሆንም ወደ መካከለኛዉ ምስራቅ በተለያዩ ምክንያቶች የሰዎች ዝዉዉር በመኖሩ በሽታው በማንኛውም ጊዜ ወደ ሀገራችን ሊገባ ይችላል።

ስለሆነም እርስዎም ሆኑ ቤተሰብዎ በማንኛውም ወቅት ለበሽታው ሊጋለጡ ስለሚችሉ ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግና እንዳይያዙ መከላከል አስፈላጊ ነው።

## 2 በበሽታው የተያዘው ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶችና ስሜቶች ምንድን ናቸው?

በበሽታው የተጠቁ አብዘኛዎች ሰዎች ቀላል ጉንፋን መሰል ምልክት ያሳያሉ። የተወሰኑት ሰዎች ግን በጠና የሚታመሙ ሲሆን የሚከተሉትን ምልክቶች ያሳያሉ፤

- ትኩሳት፣
- አጣዳፊና ከፍተኛ የመተንፈሻ አካል ህመም
- ሳልና
- የትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ ማለትና የመተንፈስ ችግር ሁሉም ህመምተኞች ላይ ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን በብዙ ህመምተኞች ላይ የሳንባ ምች ምልክቶች፣ የተቅማጥና የሆድ ውስጥ ህመም ስሜት ሊታይባቸው ይችላል።

## 3 የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov) እንዴት ይተላለፋል?

- የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ የሚተላለፈው በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር በቅርበት በሚደረግ ንኪኪ ነው።
- የታመሙ ሰዎች በሚያስሉበትና በሚያስነጥሱበት ጊዜ የሚወጣውን ቫይረስ ያለበትን አየር ወደ ውስጥ በመሳብ እንዲሁም በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ጋር በመጨባበጥ እና እነርሱ የነኩትን የበር እጀታ ፣ ቁልፍ ፣ ስልክ እና የመሳሰሉ እቃዎችን በመንካት ሊተላለፍ ይችላል።
- በሽታው ካለበት ግመል ወደ ሰው እንዲሁም ያልበሰሉ ምግቦችና የእንስሳት ተዋፅዖ መመገብ በሽታውን ያስተላልፋሉ።

## 4 የመካከለኛው ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ መድኃኒት አለው?

ይህ በሽታ ለጊዜው ፈዋሽ የሆነ መድኃኒትም ሆነ ክትባት የለውም ፤ ቢሆንም ግን በሽታውን መከላከል ግን ይቻላል።

## 5 በሽታውን እንዴት ልንከላከል እንችላለን?

- ማንኛውም ሰው ሁል ጊዜ በተለይም ደግሞ ካስነጠሰው እና ካሳለው በኋላ እጁን በውሃና በሳሙና በደንብ መታጠብ አለበት፤
- በሚያስነጥሱበት እና በሚያስሉበት ወቅት አፍንና አፍንጫን በመሐረብ ወይም በጨርቅ መሸፈን በተጨማሪም ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽንና አክታን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ መጣል፤
- አይንን ፣ አፍንና አፍንጫን ከመነካከት መቆጠብ፤
- ከታመሙ ሰዎች ጋር የቅርብ ንኪኪ ከማድረግ መቆጠብ እንዲሁም የመመገቢያ ዕቃዎችን በጋራ አለመጠቀም፣
- እንደ የበር እና የስልክ እጀታ እንዲሁም ቁልፍ የመሳሰሉና ብዙ ጊዜ በእጅ የሚነካኩ እቃዎችን በየጊዜው ማፅዳት፤ መስኮቶችን ሁል ጊዜ በመክፈት በቂ አየር ኢንዲገባ ማድረግ፤
- ጥሬ ስጋ ወይም በደንብ ያልበሰለ ምግብ እንዲሁም ያልፈላ የግመል ወተት አለመጠጣት። አትክልትና ፍራፍሬ ከመመገብዎ በፊት በደንብ መታጠቡን ማረጋገጥ።
- ማንኛዋም ሴት የበሽታው ምልክት ከታየ ለልጅ ጡት ከማጥባት ወይም ከመመገብ በፊት አፍንና አፍንጫን መሸፈን ፤ እንዲሁም እጅን በሳሙናና በውሃ በደንብ መታጠብ አለበት፤
- የስኳር በሽታ ፣ የቆየ የሳንባ ህመም ፣ የደም ግፊት ፣ የልብ ድካም እንዲሁም ከአቅም መዳከም ጋር የተያያዙ በሽታዎች ያለባቸው ሰዎች የሰውነት የመከላከል አቅማቸው የሚያዳከም በመሆኑ ለመካከለኛ ምስራቅ የመተንፈሻ አካል በሽታ (MERS-Cov) በቀላሉ ሊጋለጡና ሊጠቁ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።